# የ1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ ጥናት

## መግቢያ

- የ1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ እንዲሁም የቲቶ መልዕክት በተለምዶ *"መልእክታተ ምጋቤ"* ተብለው ይጠራሉ፡፡

- ይህ ስያሜ የተሰጣቸው አጥቢያ ቤተክርስቲያንን በመጋቢነት እንዲያገለግሉ ኃላፊነትን ለተረከቡ ግለሰቦች (ለጢሞቴዎስ እና ለቲቶ) የተጻፉ በመሆናቸው ነው።

- ከስሙ እንደምንረዳው 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የላከው መልእክት ነው፡፡

- ጢሞቴዎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መመላለስ እንዳለበት፣ የእግዚአብሔን ቤት እንዴት ማስተዳደር እንደሚገባው እና ምዕመኑም እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ በሰፊው ሲመክረው እንመለከታለን።

## 1. የመልዕክቱ ጸሃፊ፡-

- በሁለቱም መልዕክቶች መክፈቻ ላይ በግልጽ እንደምንመለከተው የመልዕክቱ ጸሐፊ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲሆን የመልዕክቱ ተቀባይ ጢሞቴዎስ እንደሆነ እንገነዘባለን (1ኛ ጢሞ.1፡1-2፣ 2ኛ ጢሞ. 1፡1) ።

- ጸሐፊው ጳውሎስ፣ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደምንረዳው፣ በመጀመሪያ በቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ እና የክርስቲያኖች ቀንደኛ ጠላት ነበር፤

- ጌታ ሲገናኘው፣ ሙሉ በሙሉ ተለውጦ እስከ ሞት ድረስ ለጌታ እውነት የሚታገል ቅን ወታደር ሆኗል።

- በዚሁ መልዕክት ውስጥ ጳውሎስ ይህንን የሕይወቱን ታሪክ አጠር አድርጎ ሲተርክ "አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም ብሆን፣ ይህን አደረገልኝ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ" ብሏል( 1ኛ ጢሞ. 1፡13)።

## 2. የመልዕክቱ ተቀባይ፡-

- የመልዕክቱ ተቀባይ የሆነው ጢሞቴዎስ በሌላ በኩል፣ ከልጅነቱ ጀምሮ የጌታን ቃል እየተማረ ያደገ ወጣት ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡14-15) ።

- ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኘው በጌታ የሚተጋ እና በአካባቢው የነበሩ ክርስቲያኖች የሚመሰክሩለት ትጉ ደቀ መዝሙር ነበር (ሐዋ. 16፡1) ።

- ጳውሎስም ምስክርነቱን ከሰማ በኋላ ጢሞቴዎስን ገርዞ ከእርሱ ጋር በአገልግሎቱ እንዲካፈል መንገድ ከፍቶለታል።

- በዚህም መሠረት ጢሞቴዎስ ለሐዋሪያው ጳውሎስ እንደ ቀኝ እጅ በመሆን አብሮት አገልግሏል።

- ከዚህም በላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ በጢሞቴዎስ አገልግሎት እጅግ በመርካቱ፣ "በእምነት እውነተኛ ልጄ" (1ኛ ጢሞ. 1፡1-2)፣ እና "ለተወደደው ልጄ" (2ኛ ጢሞ. 1፡1-2) እያለ

በቁልምጫ ከመጥራት አልፎ፣ “ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንዳገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ” (ፊል. 2፡22) ሲል መስክሮለታል።

- *በአጭሩ የጢሞቴዎስ መልዕክት፣ ድሮ ክርቲያኖችን ያሳድድ የነበረ አንድ አመፀኛ ሰው እና በእግዚአብሔር ቃል ያደገ አንድ ወጣት በጌታ ምክንያት ተገናኝተው እንደ አባትና ልጅ ሆነው በሚያገለግሉ ሁለት ግለሰቦች ግንኙነት ምክንያት የተገኘ መልዕክት ነው።*

## 3. መልዕክቱ የተጻፈበት ጊዜ

- በሐዋርያት ሥራ 28፡30-31 ተጽፎ እንደምንመለከተው፣ ጳውሎስ በሮም እስረኛ ሆኖ ተከራይቶ በሚኖርበት ቤት ውስጥ ሆኖ ሊጎበኙት የሚመጡትን ያለመከልከል ወንጌልን ለሁለት አመት እየሰበከ ያስተምራቸው ነበር።

- ሆኖም ታሪክ እንደሚያስረዳው፣ ከሁለት ዓመት በኃላ፣ ከሮም እስረኝነቱ ተፈትቶ እንደገና ወንጌልን እየሰበከ ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ነበር።

- በዚህ አጋጣሚ ሐዋሪያው ከኤፌሶን ወደ መቄዶኒያ ሲያመራ ቤተ ክርስቲያኗ ጠንካራ የመጋቢ አመራር ያስፈልጋት ነበርና፣ ጢሞቴዎስን በኤፌሶን እንዲያገለግል ትቶት ይሄዳል፤

- ሆኖም ጢሞቴዎስ ወጣት እንደመሆኑ መጠን በቤተ ክርስቲያን አመራር ዙሪያ ብዙ ሊያውቃቸው የሚገባ ነገሮች ነበሩና፡ ሐዋሪያው መቄዶንያ ሲደርስ የመጀመሪያውን መልዕክት ለጢሞቴዎስ ይልካል (1ኛ ጢሞ. 1፡3) ።

  - *በዚህ መሠረት 1ኛ ጢሞቴዎስ የተጻፈው <u>ከ65-66</u> ባለው ዓመተ ምህረት ውስጥ እንደሆነ ይታሰባል።*

- 2ኛ ጢሞቴዎስ በሌላ በኩል የተጻፈው ሐዋሪያው እንደገና በሮም እስረኛ ከሆነ በኃላ የሞት ፍርዱን ይጠባበቅ በነበረበት ጊዜ ነው (2ኛ ጢሞ. 4፡6-8) ።

- የታሪክ መረጃ እንደሚያስረዳው ጳውሎስ ሰማዕት ሆኖ ያለፈው ኔሮ የተባለ የሮም ቄሳር ይገዛ በነበረበት ጊዜ <u>*በ67*</u> ዓመት ምህረት ነው።

  - *ይህንን እውነት በመደገፍ 2ኛ ጢሞቴዎስ የተጻፈው <u>ከ66-67</u> ባለው ጊዜ እንደሆነ መረዳት እንችላለን።*

## 4. የመልዕክቱ ዋና አላማ

- ከመልዕክቱ ከራሱ ልንረዳው እንደምንችለው፣ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተነሱ ሃሰተኛ አስተማሪዎች ነበሩ። (1 ጢሞ. 1፡3)

- በትምህርታቸው ስለ ህግ ተገቢ ያልሆነ አመለካከትን የሚያስተምሩ መናፍቃን ነበሩ።

- ከዚህም በላይ ከአስተማሪዎቻቸው ሁለቱ ሄሜኔዎስ እና እስክንድሮስ የሚባሉ ነበሩ (1 ጢሞ. 1፡20)

- አስተምህሮአቸው እንዲያው የሰው ፈጠራ ብቻ ሳይሆን በዲያቢሎስ የተቀናበረ ትምህርትም ነበር (1 ጢሞ. 4፡1-2)

- በዚህም አደገኛ አስተምህሮአቸው መሠረት ጋብቻን ከመከልከላቸው ባሻገር፣ የተወሰኑ ምግቦችን ሰዎች እንዳይበሉ ያዙ ነበር (4፡3)
- እንዲሁም የእውነተኛ መንፈሳዊነት መለኪያ ምድራዊ ትርፍ እንደሆነ ያሳስቡ ነበር (1ኛ ጢሞ. 6: 9-10)።

## ❖ 1ኛ ጢሞቴዎስ

- ሐዋሪያው፣ ጢሞቴዎስን በኤፌሶን እንዲቀመጥ ያዘዘበት ዋነኛ ምክንያት እንዲህ ያለውን ትምህርት የሚያስተምሩትን ሰዎች እንዲከላከል ነበር። (1ኛ ጢሞ 1፡3)

- ሐዋሪያውም 1ኛ ጢሞቴዎስን የጻፈበት ሌላው ምክንያት፣ እንዲህ ካለው ኑፋቄ ራሱና የእግዚአብሔርን መንጋ በእግዚአብሔር ቃል እንዲጠብቅ ሲሆን

- ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ አገልግሎት እንዴት መሆን እንዳለበት እንዲሁም ለአገልግሎት የሚሾሙት ሰዎች እንዴት ያሉ መሆን እንዳለባቸው ያሳስባል።

## ❖ 2ኛ ጢሞቴዎስ

❖ የኑፋቄ አስተማሪዎቹ ለሰው የወንጌል ቁልፍ የሆነውን የትንሳኤ አስተምህሮ ክደው "ትንሣኤ ሙታን ከዚህ በፊት ሆኖአል እያሉ የአንዳንዶቹን እምነት" እስከመገልበጥ ደርሰዋል (2ኛ ጢሞ. 2፡18) ።

- ስለዚህ ሐዋሪያው በአንድ በኩል ስለነዚህ መናፍቃን ስለ ትምሕርታቸው ይዘት ጢሞቴዎስን ያሳስበዋል።

- በሌላ በኩል ደግሞ ጳውሎስ በእስር ላይ ሆኖ ሳለ ከሉቃስ በስተቀር (2ኛ ጢሞ. 4፡11) በአጠገቡ ማንም እንደሌለ ይነግረዋል።

- በጌታ እውነተኛ ልጁ የሆነው ጢሞቴዎስም ስለናፈቀው፣ በቶሎ ወደ እርሱ እንዲመጣ ያሳስበዋል፣

- እንዲሁም፣ በጊዜው በነበረው ስደት ምክንያት በጌታ መጽናት ምንም ከባድ ቢሆን በወንጌል እንዲጸና እና አስፈላጊውን መከራ እንዲቀበል ይመክረዋል(2ኛ ጢሞ. 1፡8፣ 2፡3፣ 4፡5)።

# ጥናት አንድ

## *ከሃሳዊ አስተምህሮ እንጠበቅ...*

**የምንባብ ክፍል፦ 1ኛ ጢሞ.1፡1-20**

*መግቢያ፦*

*ሐዋሪያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የሀሰት አስተማሪዎች ወደፊት እንደሚመጡ አስመልክቶ ነበር። (ሐዋ 20፡28-30) ፣ ከብዙ አመታት በኋላ የተለየ ትምህርት የሚያስተምሩ አሳቾች ወደ ቤተክርስቲያኒቱ መግባታቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስገነዝበናል። ሆኖም ግን እነዚህን የሃሰት አስተማሪዎች ለመከላከልና እውነተኛውን አስተምህሮ በቤተክርስቲያን ለመጠበቅ እንዲቻል ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ ኤፌሶን ይልከዋል። በዛሬው ጥናታችን ጳውሎስ ስለ አስተማሪዎቹ ማንነት እና ስለ አስተምህሮአቸው የጻፈውን እንመለከታለን።*

*ዓላማው፦*

*እንደ ታማኝ ክርስቲያን ራስን እና ሌሎችን ከሃሳዊ አስተምህሮ ለመጠበቅ፣ እንዴት እንደምንችል ለመገንዘብ።*

1. ከሰላምታው አሳብ በመነሳት፣
   - ስለ ጸሐፊው እና ስለ መልዕክቱ ተቀባይ ማንነት ምን እንረዳለን? (የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት ሐዋ 16፡1-4 ያለውን ይመልከቱ።)
   - ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ጌታ ኢየሱስ የተሰጡት ገላጭ ቃላት ምን ያስገነዝቡናል?
2. በቁ. 3-4 መሠረት ጢሞቴዎስ በኤፌሶን በነበረችው አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲቀመጥ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ለምንድን ነው?
3. በኤፌሶን የነበረችው ቤተክርስቲያን፣ በዘመኗ የገጠማት ሃሳዊ አስተምህሮ ምን ይመስል ነበር?
   - (ከቁ. 4-7 ያለውን ይመልከቱ)።
4. በቁ. 6-7 መሠረት ስለ ሃሰተኛ አስተማሪዎቹ ማንነት የምንገነዘበው ምንድነው?
   - የአስተምህሮአቸው ይዘት ምን ይመስላል (ቁ.3-4)?
5. አሁን ባለንበት ዘመን እውነት የሚመስሉ አሳች ትምህርቶችን ሰዎች በስህተት ሲከተሉ አጋጥሞህ ያውቃል?
   - ከሆነ፣ የትምህርቱ ይዘት ምን ነበር?
   - ተከታዮቹስ እንዴት ሊስቱ ቻሉ?
6. ከቁ. 8-11 መሠረት
   - ጳውሎስ በዚህ ክፍል ስለ ህግ መናገር ለምን አስፈለገው?

- ከቁ. 6-7 ካለው ክፍል ጋርስ ምን ያዛምደዋል?

7. በቁ. 12 ላይ ህግ መልካም እንደሆነ ጳውሎስ ያስረዳል
   - በህግ መዳን እንደሚቻል ለማመልከት ነው ወይስ ሌላ ትርጉም አለው?
   - ሌላ ትርጉም ካለው ከቁ. 15-16 ባለው መሠረት ድነት (salvation) የሚገኘው በምንድን ነው?
8. ከላይ እንደተመለከትነው የሃሰት አስተማሪዎቹ የህግን ትምህርት ማስተማር ይወዳሉ።
   - በቁ. 12-17 መሠረት ጳውሎስን ከእነዚህ አስተማሪዎች የሚለየው ምንድን ነው?
9. በቁ. 18-19 መሠረት በክርስትና ውስጥ ጥሩ ተጋድሎ (መልካም ጦርነት) ለማበርከት እንዲችል ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ሁለት አደራዎች ምንድን ናቸው?
10. ቁ. 19ን በመመልከት ጳውሎስ በጎ ህሊናን እና እምነትን የመሰለው በምንድን ነው?
    - በሕይወታችን ከሁለቱ አንዱን ማጣት የሚያመጣውስ ጉዳት ምን ይመስላል?
11. በቁ. 20 መሠረት የሀሰት አስተማሪዎቹ የጎደላቸው የትኛው ነበር?
12. በዚህ ዘመን ሐሰተኛ አስተምህሮዎች በምን አይነት መንገድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ ይችላል ብለህ ታስባለህ?
13. ቁ. 5 እንዲሁም 19ን በመደገፍ ከእንደዚህ ዓይነት አደጋ አንተንም ሆነ ሌሎችን ለመጠበቅ ልትወስደው የሚገባ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

# ጥናት ሁለት

## *እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ*

**የምንባብ ክፍል፦ 1ኛ ጢሞ. 2፥1-15**

***መግቢያ፦***

*ሰው እግዚአብሔርን የሚያመልከው እግዚአብሔር በሚፈልገው መልኩ እንጂ አምላኪው ግለሰብ በፈለገው መንገድ አይደለም። እግዚአብሔርን እንዴት ልናመልክ እንደሚገባ በቃሉ በተለያየ መንገድ ተገልጾአል። በዚህ ክፍል በሕብረት ስናመልክ እና ስንፀልይ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ እንዴት እንደሆነ እንመለከታለን።*

***ዓላማው፦***

*እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ ምን መሆን እንዳለበትና እንዴትም ይህንን እውነት ተግባራዊ ማድረግ እንደምንችል ለመገንዘብ።*

***ከቁ 1-7 ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ በሚፈልገው እና ለሰው ሁሉ መዳን የሚሆነውን ጌታን በሰጠው በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ፣ በአምልኮአችን ጊዜ ስለ ሰዎች ሁሉ እንድንጸልይ ሐዋሪያው ያሳባል።***

- በቁ. 1 እና 2 መሠረት በጸሎታችን ውስጥ ልናካትት የሚገቡን እውነቶች ምንድናቸው?

- በቁ.1-2 መሠረት ለባለስልጣናት ጸሎት ማቅረብ በመንፈሳዊውም ሆነ በአካላዊ ኑሮአችን ላይ አስተዋጽኦ የሚያደርገው እንዴት ነው?

  ለዚህስ ምሳሌ ማቅረብ ትችላለህ?

3. በቁ. 1-2 ባየነው መሠረት ጸሎት ማድረግ ያለብን ለባለ ስልጣናት ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ ነው።

   በቁ. 3 እና 4 ለሠዎች ሁሉ ለምን መጸለይ እንዳለብን የተሰጡ ሁለት ምክንያቶች ምንድናቸው?

   (ሁለቱ ምክንያቶች በአዲሱ መደበኛ ትርጉም በግልጽ የተቀመጡ በመሆናቸው አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ማገናዘቡ ይረዳል።)

4. በቁ 6 እና 7 መሠረት ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ የሚወደው እግዚአብሔር ሰው ሁሉ መዳን እንዲችል ምን አድርጎአል? (ሁለት ምክንያቶች)

- በቁ. 5 ላይ በተጻፈው መሠረት ጌታ ኢየሱስ በኃጢአተኛ ሰው እና በቅዱሱ በእግዚአብሔር መካከል መሆን ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው?

  መካከል ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?

  ይህስ የክርስቶስን አምላክነት ያሳንሳል ማለት ነው?

***ከቁ. 8-15 ባለው ጳውሎስ በሕብረት ጸሎት እና አምልኮ ጊዜ ወንዶች እና ሴቶች እንዴት ባለ ሁኔታ መቅረብ እንዳለባቸው ያስገነዝባል።***

- በቁ. 8 ላይ ለወንድሞች የተሰጠው ማሳሰቢያ ምንድን ነው?

- በቁ. 8 ላይ በተሰጠው በዚህ ማሳሰቢያ መሠረት፣ በአምልኮም ሆነ በጸሎት ጊዜ እጃችንን ከማንሳት፣ ከመንበርከክ፣ አይኖቻችንን ከመጨፈን፣ ራሶቻችንን ወደ ሠማይ ከማንሳት ወይም ወደ ምድር ዝቅ ከማድረግ ሁሉ በላይ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?

- ከቁ.9-10 ያለውን በመደገፍ፣ ለሴቶች የተሰጠው ማሳሰሰቢያ ምንድን ነው?

  በዚህ ክፍል መሠረት ሴቶች ሊዋቡ አይገባም ማለት ነው?

- ከቁ. 11-14 ባለው ክፍል መሠረት ሴት ከወንድ ጋር ሊኖራት የሚገባው ግንኙነት የተገለጸው እንዴት ነው?

  ሴት ከወንድ ከመስማት እና ከመገዛት በስተቀር የራስዋን ስሜት መናገር መብት የላትም ማለት ነው?

  ወይስ ሴት ከወንድ ታንሳለች ማለት ነው?

- ሴት በመውለድ ትድናለች ሲል ምን ማለት ነው?

  ድነት በጌታ በማመን ነው ወይስ ልጅ በመውለድ?

- በክፍሉ መሠረት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ ምን አይነት ነው?

  እኛስ በሕይወታችን ልናደርገው ስለሚገባን ተቀዳሚ ተግባር የሚያስተምረን ምንድነው?

# ጥናት ሦስት

## *የመልካም አገልጋይ አካሄድ*

**የምንባባ ክፍል፦ 1ኛ ጢሞ 3፡1-16**

***መግቢያ፦***

*ለአገር ሕዝብ መሪ፣ ለኳስ ተጫዋች ቡድን አሰልጣኝ እና አምበል፣ ለመስሪያ ቤት ሠራተኞች ዋነኛ ተጠሪ እንዳላቸው ሁሉ፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ደግሞ ለእግዚአብሔር ህዝብ መሪ አለው። መሪ የሌለው ህዝብም ሆነ ቡድን ወይም ማኅበር ማድረግ የሚጠበቅበትን አያውቅም፣ ስለዚህም መና ይቀራል፣ ብሎም አንድ ቀን ይበተናል። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስንመጣ እውነት፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መሪ መስጠት ብቻ ሳይሆን የመሪነት ቦታ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ሰዎች እንዴት መሆን እንዴት መኖር እንደሚገባቸው በዛሬው ጥናታችን ይህንን በተመለከት በሰፊው እንመለከታለን።*

***ዓላማው፦***

*ቤተክርስቲያንን በመምራትና በማገልገል የሚሳተፉ ሰዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ መልካም ባህርይ ምን መሆን እንዳለበት ለመገንዘብ።*

*ከቁ.1-7 ባለው ክፍል የቤተ ክርስቲያን እረኞች ወደ አገልግሎቱ ሲመጡ ሊኖራቸው የሚገባውን ሕይወት ሲያሳይ፣ ከ ቁ.8-13 ባለው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት ሊታይባቸው የሚገባውን ክርስቲያናዊ አካሄድ ይዘረዝራል።*

- በቁ.1 ላይ "ኤጲስ ቆጶስ" የሚል ቃል እንመለከታለን።

  ኤጲስ ቆጶስ ምን ማለት ነው?

  በቲቶ 1፡5-7 ያለው ክፍል ስለ ኤጲስ ቆጶስ ምንነት ሊያሳይህ የሚችለው ነገር አለ?

  በ1ኛ ጴጥ.5፡1-5 ያለው ክፍል የሚናገረውስ ስለ ምንድነው?

- በሐዋ. 20፡17 ላይ የተጠቀሱት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ በቁጥር 28 መሠረት ሌላ የተሰጣቸው ስም ምንድነው?

  (የቀደመውን እና አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ያወዳድሩ)

- ከላይ እንዳየነው፣ ኤጲስ ቆጶስ ማለት ሽማግሌ፣ ጠባቂ፣ መጋቢ እንዲሁም እረኛ ማለት ከሆነ፣

  ከስሙ ብቻ በመነሳት፣ የኤጲስ ቆጶስ አገልግሎት ምንድን ነው ትላለህ?

  (ሐዋ. 20፡28 እና 1ኛ ጴጥ. 5፡1-  ያለውን በድጋሚ ተመልከቱ)

- በሐዋ. 20፡28 ላይ እንደምናየው፣ በኤፌሶን የነበሩትን ሽማግሌዎች የሾማቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ መጽሐፉ ያስገነዝበናል፣ በዚህ ክፍል ግን "ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ" ይላል።

  ለዚህ አገልግሎት የሚያበቃው ጥሪ ነው፣ ወይስ ፍላጎት?

  ሁለቱስ ክፍል የሚቃረኑ ናቸው ወይስ… ?

- በቁ. 2 ኤጲስ ቆጶስ (የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ/እረኛ) የማይነቀፍ ሊሆን እንደሚገባው ይነግረናል።

  ይህ ማለት ከቶ ኃጢአት የማይሰራ ለማለት ነው ወይስ …?

- በቁ. 4 የእግዚአብሔር ቤት ሽማግሌ ልጆቹን እና ቤተሰቡን በአጠቃላይ በመልካም የሚያስተዳድር ሊሆን የሚገባው ለምንድን ነው?

  (ቁ. 5 ላይ የተሰጠውን ምክንያት ይመልከቱ!)

- በቁ. 5 ቤትን በሥነ ስርዓት መያዝን እና አገልገሎትን የሚያገናኛቸው ነገር ምንድን ነው?

  ይህስ አገልግሎት  የሚጀምረው ከየት እንደሆነ ያስተምረናል?

- በቁ. 6 እና 7 መሠረት የቤተክርስቲያን መሪ አዲስ ክርስቲያን ሊሆን የማይገባው ለምንድን ነው?

- ከላይ እንዳየነው፣ ከቁ. 8-13 የዲያቆናት አካሄድ እንዴት እንደሆነ ከመመልከታችን አስቀድሞ፡

  ሐዋ 6፡1-6ን  በመመልከት

    የዲያቆናት አገልግሎት የተጀመረው መቼ ነው?

    አገልግሎቱስ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ምንድነው?

    አካሄዳቸውስ እንዴት ሊሆን ይገባል?

    አገልግሎታቸው ከሽማግሌዎችስ አገልግሎት በምን ይለያል? ቁ.8-13

- በቁ. 9 መሠረት "የሃይማኖትን ምሥጢር ሊይዙ ይገባቸዋል" ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል?

- በቁ 13 መሠረት በእውነት እና በመልካም ሁኔታ ያገለገሉ ዲያቆናት ዋጋ ምንድን ነው?

**ከቁ. 14-16 ባለው ሐዋሪያው ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያንን ምንነት እና የአስተምህሮዋን መሰረት በአጭሩ ይገልጻል።**

- አዲሱ መደበኛ ትርጉምን በመደገፍ፣ ጳውሎስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን የገለጸበት ሦስት ስሞች ምንድን ናቸው?

    ስለቤተክርስቲያንስ ምንነት ምን ያስተምሩናል?

- ቤተ ክርስቲያን የእውነት አምድ እና መሠረት ተብላ ተጠርታለች።

    በቁ.16 መሠረት ያ እውነት ምንድን ነው?

14. ቤተክርስቲያንን በመምራትና በማገልገል የሚሳተፉ ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባ ባህርይ ምን ሊሆን እንደሚገባ የተረዳኸውን ግለጽ

# ጥናት አራት

## *የክርስቶስ ኢየሱስ በጎ አገልጋይ*

**የንባብ ክፍል፦ 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1-16**

*መግቢያ፦*

*በሰው ዘንድ ሰነፍ እና በጎ ባርያ ወይም አገልጋይ እንዳለ ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥም እንዲህ ነው። ሰነፉ አገልጋይ ለአገልግሎቱ ግድ የማይለው፣ ነገ ለሚጠፋው ምድራዊ ሕይወቱ ብቻ ሲያስብ አገልግሎቱን ይዘነጋና "ሃኬተኛ ባሪያ" ይሆናል። እግዚአብሔርን የሚፈራና አገልግሎቱን የሚያከብረው ግን እንደ ጳውሎስ በሕይወቱ ፍጻሜ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ!" ለማለት ድፍረት ያገኛል፤ እግዚአብሔርም ለዳዊት እንዳለው "እንደ ልቤ የሆነ ሰው" ይለዋል። በዛሬው ጥናታችን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ በጎ አገልጋይ እንዴት ያለ እንደሆነ እንመለከታለን።*

*ዓላማው፦*

*እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ በጎ አገልጋይ ሊኖረው የሚገባውን ሕይወት እና አካሄድ ምን ሊሆን እንደሚገባ ለመገንዘብ።*

***ከቁ.1-5 ባለው ክፍል፣ በዘመን መጨረሻ ስለሚመጡ የሀሰት አስተማሪዎች በመናገር፣ የትምህርታቸው ምንጭ አጋንንት እንደሆኑ እና የትምህርታቸውም ይዘት ከእግዚአብሔር ቃል የራቀ መሆኑን ይዘግባል።***

- በቁ. 1 መሠረት፣ የሀሰት አስተማሪዎቹ የሚከተሉትን ትምህርት የሚያመጡት ከየት ነው?

  የሚሰሙትንስ የስህተት ትምህርት እንዴት ተቀብለውት ሊኖሩ ቻሉ?

  (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ቁ. 2ን ይመልከቱ)

- በቁ. 3 መሠረት የዚህ የስህተት ትምህርት ይዘት ምንድን ነው?

  ትምህርቱንስ ስህተት ያሰኘው ምንድን ነው (ቁ.4ን ይመልከቱ)።

- እስከ አሁን ካየነው በመነሳት፣ አሁን በዘመናችን የሚናፈሱት የስህተት ትምህትቶች ምንጭ ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

  ስህተት መሆናቸውንስ መመዘኛው ምንድን ነው?

**ከቁ.6-16 ባለው ክፍል፣ እንደ እግዚአብሔር በጎ አገልጋይ፣ በሕይወቱ እንዴት ሊመላለስ እንደሚገባው፣ ለሌሎችም እንዴት እና በምን ምሳሌ ሊሆን እንደሚገባው እንዲሁም ምን ማስተማር እንዳለበት ሐዋሪያው ጢሞቴዎስ ያሳስበዋል።**

- በቁ.6 መሠረት፣ ጢሞቴዎስ የክርስቶስ ኢየሱስ መልካም አገልጋይ ለመሆን ለወንድሞች ማሳሰብ ያለበት ነገር ምንድን ነው?

- ቁ.7ን በመመርኮዝ፣ በጎ አገልጋይ ሊርቀውና ሊይዘው የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

- ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እግዚአብሔርን መምሰል እንዲለማመድ ያሳስበዋል (ቁ.7) ።

  በዚህ መሠረት እግዚአብሔርን መምሰል ምን ማለት ነው?

  ሰውስ እግዚአብሔርን መምሰል የሚችለው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔርን መምሰል ከአካል ብቃት ልምምድ (Sport) ይልቅ ሊበልጥ የቻለው እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ (ቁ.8ን ይመልከቱ)?

- በቁ.10 ላይ እንደምናየው፣ ሐዋሪያው እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ሲሉ እንደሚደክሙና እንደሚሰደቡ ይገልጻል ።

  በመድከም፣ በመሰደብ እንዲሁም በመሰደድ ሁሉ ውስጥ ተስፋ ሳይቆርጡ እግዚአብሔርን ለመምሰል እንዲጥሩ የሚያደርጋቸው ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?
  (ቁ.10ን በሚገባ ይመልከቱ!)

- በቁ.11 እና 12 ላይ ጢሞቴዎስ እንደ በጎ አገልጋይ ለሌሎች ምሳሌ መሆን እንዳለበት ጳውሎስ ያሳስበዋል።

  በምን እና እንዴት ነው ምሳሌ እንዲሆን የሚያሳስበው?

  ምን ማለት እንደሆኑም ያብራሩት!

- ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ማንም ታናሽነቱን እንዳይንቀው ሲያዘው እናያለን፤ ግን ጢሞቴዎስ ታናሽነቱ ሳይመለከት ራሱን ሊያስከብር የሚችለው እንዴት ነው?

- በቁ. 16 መሠረት በጎ አገልጋይ በመጀመሪያ ራሱን ብሎም የሚሰሙትን ማዳን እንዲችል ሊያደርገው የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

- እስከ አሁን ካየነው በመነሳት በጎ አገልጋይ ሊኖሩት የሚገቡ ባህሪያት ምንድናቸው?

- እነዚህን በመፈጸሙስ በሕይወቱ የሚመጣው ለውጥና በረከት ምንድነው?

- ይህን መረዳትህ በሕይወትህ ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን የሚገባው ነገር ምንድነው?

# ጥናት አምስት

## ***የእግዚአብሔርን ቤት ሰዎች አያያዝ***

***የምንባባ ክፍል፦ 1ኛ ጢሞ. 5፡1-6፡2***

***መግቢያ፦***

*ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚጨመሩትን አባላቶችዋን መጽሐፍ ቅዱስ ከማስተማር በላይ የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሠረት ልታስተናግዳቸው ይገባል። በዛሬው ጥናታችን 1ኛ ጢሞ.5፡1-24 ያለውን በመደገፍ የተለያዩ የቤተክርስቲያን አባላት ሊሰጣቸው የሚገባውን ስፍራ እና አያያዝ እንመለከታለን።*

***ዓላማው፦***

*በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታቀፉት አባላት እንዴት ልንይዛቸው እንደሚገባ ለማወቅ እና እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት እንዴት እንድናስተናግዳቸው እንደሚገባ ለመገንዘብ።*

***ከቁ. 1-2 ባለው ክፍል፣ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ቤተ ክርስቲያን ልትሰጠው የሚገባውን መስተንግዶ ካሳሰበ በኋላ ከቁ.3-16 ትኩረቱን በባልቴቶች ላይ በማተኮር ባልቴት የሚባሉት ሴቶች ምን አይነት እንደሆኑ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ሙሉ እንክብካቤ ልትሰጣቸው የሚገባው እንዴት ያሉትን ባልቴት እንደሆነ ያስገነዝባል።***

5. ከቁ. 1-2 ባለው ክፍል፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያንን አባላት የከፈላቸው በስንት ቡድን ነው?

   ጢሞቴዎስስ እንደ መጋቢ እንዴት እንዲያስተናግዳቸው ነው የተጠየቀው?

6. በቁ. 3 ላይ ጢሞቴዎስ ባልቴቶችን እንዲያከብር ተነግሮታል።

   ባልቴት የሚባሉት እንዴት ያሉ ሴቶች ናቸው?

7. ቁ. 4 እና 5ን በመመርኮዝ ጢሞቴዎስ በቁ. 3 ላይ እንዲያከብራቸው የተጠየቀው እውነተኛ ባልቴቶች (በእርግጥ የተቸገሩ ባልቴቶች) እንዴት ያሉት ናቸው?

   የተቸገሩ ባልቴት ያሰኛቸውስ ምንድን ነው?

   ያልተቸገሩትስ?

8. ቁ.4ን እንዲሁም 16ን በመደገፍ፣ ባልቴቶች ልጆች ካሏቸው፣ ከልጆቻቸው ወይም ከልጅ ልጆቻችው የሚጠበቅባቸው ምንድን ነው?

   ይህንን ኃላፊነት የማይወጣ ሰው ምን አይነት ሰው ነው (ቁ.8 ይመልከቱ)?

9. ከቁ. 9-11 ባለው ክፍል ባልቴቶችን በሁለት ይከፍላቸዋል። በነዚህ በሁለቱ ባልቴቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

10. አሁን ባለንበት ዘመን (በተለይም nursing home እንዲሁም social security benefit ሊገኝ በሚችልበት ቦታ) ቤተክርስቲያን ይህንን ለባልቴቶች ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት እንዴት ልትፈጽም ትችላለች ብለህ ታስባለህ?

**ከቁ.17-25 ባለው ክፍል በቤተክርስቲያን ውስጥ በሽማግሌነት የሚያገለግሉ ሰዎችን ጢሞቴዎስ እንዴት ሊያስተናግዳቸው እንደሚገባ መመሪያ ይሰጣል።**

11. በቁ 17 እና 18 መሠረት፣ በመልካም የሚያስተዳድሩ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ ሽማግሌዎች ሊከበሩ የሚገባቸው በምን ምክንያት ነው?

    (በቁ. 18 ላይ የተሰጠውን ምክንያት ልብ ብለው ይመልከቱ)

12. በቁ 17 ላይ በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ሲል፣ በመልካም የማያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያስገነዝባል ብለህ ታስባለህ?

    ቁ.19 በመመልከት ለዚህ መልስ ሊሰጥህ የሚችለው ፍንጭ አለ?

13. በቁ. 19 መሠረት አንድ ሽማግሌ ጥፋተኛ ነው የሚባለው ስንት ምስክር ሲቀርብበት ነው (ዘዳ. 19፡15ን እንዲሁም 17፡6ን ያወዳድሩ)?

    ጥፋተኛስ ሆኖ ከተገኘ መጋቢው (ጢሞቴዎስ) ሊያደርገው የሚገባው ምንድን ነው (ለመልሱ ቁ. 20 እና 21ን ይመልከቱ)?

14. በቁ. 22 ላይ እጅን በሰዎች ላይ ፈጥኖ ስላለመጫን ይናገራል።

    1ኛ ጢሞ. 4፡14፣ 2ኛ ጢሞ 1፡6 እንዲሁም ሐዋ 13፡1-3 ያለውን በማወዳደር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጃቸውን የሚጭኑት መቼ እና ለምንድን ነው?

15. ከላይ ባየነው መሠረት፣ ጢሞቴዎስ እጁን በማንም ላይ ፈጥኖ እንዳይጭን የተከለከለው ለምን ይመስልሃል?

    እጁን ጭኖ ለአገልግሎት ከሾማቸውስ በኋላ ኃጢያትን ቢያደርጉ በቁ. 22 እና 20 መሠረት ጢሞቴዎስ ሊያደርገው የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

16. በመልካም የሚያገለግሉ እና መልካም ባለማድረጋቸው ተግሳጽ የሚገባቸው ሽማግሌዎች ሊሰጣቸው የሚገባውን አቀባበል ከተናገረ በኋላ…

    በቁ 24 እና 25 ላይ ኃጢአት ስለ ማድረግ እና መልካም ስለ ማድረግ የሚያስገነዝበው ነገር ምንድን ነው?

17. በምዕራፍ 6፡1-2 መሠረት ክርስቲያን ባሪያዎች፥ ጌቶቻቸውን ሊያከብሩ የሚገባቸው ለምንድን ነው?

18. በምዕራፍ 5፡3 እና 17 እንዲሁም ምዕራፍ 6፡1 እና 2 ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው ቃል ምንድን ነው? (በተለይ አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ይመልከቱ)።

    ይህስ ቃል በቤተክርስቲያን ውስጥ በወገኖች ግንኙነት መካከል ሊኖር የሚገባው ትልቅ ነገር ምን እንደሆነ ያመለክታል?

# ጥናት ስድስት

## *ገንዘብን የመውደድ አደገኝነት*

***የምንባብ ክፍል፦ 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡3-21***

***መግቢያ፦***

*በምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ፣ ጌታ ኢየሱስ ሰው በአንድ ጊዜ በእኩል ደረጃ ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ ሊገዛ እንደማይችል እንዲሁም ከእግዚአብሔር በላይ ገንዘብን የሚወድ ሀብታም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ እንደማይችል ተናግሯል። ይህ እውነት ገንዘብ የመውደድን አደገኛነት ያሳያል። የዛሬው ጥናት ክፍላችን ይህንን እውነት በሰፊው ያስጨብጠናል።*

***ዓላማው፦***

*ገንዘብን መውደድ አደገኛ እና የሚያጠፋ ነገር በመሆኑ፣ የሌለው ባለው ተደስቶ፣ ያለው ደግሞ ለሌላቸው እያካፈለ እና መልካም እያደረገ ሊኖር እንደሚገባው ለማሳሰብ።*

***ከቁ. 3-10 ባለው ክፍል የሀብት እና የገንዘብ ፍቀር ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ካስረዳ በኃላ፣ ከቁ.11-16 ባለው ክፍል እንዲህ ካለው የነዋይ ፍቅርን በመሸሽ፣ እንደ እግዚአብሔር ሰው በታማኝነት እንዲኖር ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ይመክረዋል።***

1. ቁ. 3ን በመመልከት አንድ ትምሕርት የስህተት ትምህርት ነው የሚባለው በውስጡ እንዴት ያለ ትምህርት ሲኖረው ነው?

2. የሀሰት ትምሕርት የሚያስተምረውን ሰው በቁ. 4 ላይ "አንዳች አያውቅም፣ ነገር ግን በትዕቢት ተነፍቶአል" ሲል ምን ማለቱ ይመስልሀል።

3. ቁ.4 እና 5ን በመመልከት፣ የሀሰት አስተማሪዎቹ ባህርይ እና የአስተምህሮአቸው ውጤት ምንድን ነው?

4. ቁ. 5 እና 6ን በማወዳደር፣ በሀሰት ትምሕርት ተከታዮች እና "ኑሮዬ ይበቃኛል" ብለው በጌታ ተደላድለው በሚኖሩ ክርስቲያኖች መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት ምንድን ነው?

   ወይም በሌላ አባባል፣ በሐሰት ትምሕርቱ ተከታዮች እና በእውነት ጌታን የሚፈልጉ ሰዎች ለገንዘብ ያላቸው አመለካከት እንዴት ነው?

5. አሁን ባለንበት ዘመንስ በጌታ የሚያምን እውነተኛ ክርስቲያን ሁሉ ሀብታም ሊሆን ይገባዋል ብለው ስለሚያስተምሩ ሰዎች ይህ ክፍል ምን ትምሕርት ይሰጠናል?

   "ኑሮዬ ይበቃኛል" ማለት ምን ማለት ይመስልሃል?

   ገንዘብ ለማግኘት እና የራሳችንን ኑሮ ከድህነት ወደ ተሻለ ኑሮ ለመለወጥ ጥረት አናደርግም ማለት ነው?

   በቁ.9 ላይ እንደምናየው፣ ባለ ጸጋ ሊሆኑ የሚፈልጉ አደጋኛ እና አጥፊ በሆነ ነገር ውስጥ እንዲገቡ ይናገራል።

በዚህ መሠረት…

ሀብታም ለመሆን መሻት ትክክል አይደለም ማለት ነው? ወይስ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለ ሌላ ነገር ነው?

በቁ. 10 መሠረት በክፉ መንገድ ሀብታም ለመሆን፡ ገንዘብን ለማግኘት መጣርን የሚጎዳ የሚያደርገው ምክንያት ምንድን ነው ?

ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሁሉ ሥር ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

እንዴትስ የኃጢአት ስር ሊሆን ይችላል?

9. ከቁ. 11-16 ያለውን በመደገፍ፣ በነዋይ ፍቅር ፈንታ ጢሞቴዎስ ምን እንዲያደርግ ነው የተመከረው? በአጭሩ አስረዳ።

*ከቁ. 17-19 ባለው ክፍል፣ ጳውሎስ በዚህ ባለንበት ዓለም ሀብታም የሆኑ ሰዎች ምድራዊ እና ጠፊ የሆነውን ገንዘብ ከማከማቸት ሁሉ በላይ፣ ሰማያዊ ሀብትን ሊያከማቹ እንደሚገባ ካሳሰበ በኋላ፣ በቀሪው ክፍል የማጠቃለያ ምክር ለጢሞቴዎስ በመስጠት ተሰናብቶ መልዕክቱን ያጠቃልላል።*

በቁ.17 መሠረት በምድራዊ ነገር ሀብታም የሆኑ ሰዎች በማን ላይ ነው ተስፋ ሊያደርጉ የሚገባው?

ለምንስ ይመስለሃል? (በምሳሌ 23፡5 ላይ በገንዘብ ተስፋ ስለ ማድረግ ከንቱነት የተጻፈውን ይመልከቱ)

11. በቁ. 18-19 ባለው መሠረት ሰው እንዴት ነው ለሚመጣው ዓለም የሚሆን መዝገብ ወይንም ሀብት ሊያከማች የሚችለው?

12. ገንዘብ ማግኘት እና ሀብታም መሆን ኃጢያት ካልሆነ፣ ለክርስቲያን ሀብታም የመሆን እና ገንዘብን የማግኘቱ ዓላማ ምን ሊሆን ነው የሚገባው ትላለህ (ቁ. 19ን እና ኤፌ. 4፡ 28ን ያወዳድሩ)?

# 2ኛ ጢሞቴዎስ

# ጥናት

## ጥናት አንድ

## *"ታማኝነት"*

**የምንባብ ክፍል፦2ኛ ጢሞ.1፡1-18**

**መግቢያ፦** *ጳውሎስ ጢሞቴዎስን፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የአገልግሎት ስጦታ እንዲያነሳሳና በተጨማሪም ካለ ፍርሃት እንዴት መኖር እንደሚገባው የጻፈለትን እንመለከታለን።*

**ዓላማው፦** *ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ስጦታ ካለ ፍርሃት እንዴት መጠቀም እንዳለብንና፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ደግሞ ሌሎችን ልንደግፍና ልናበረታታ እንዴት እንደምንችል ለመገንዘብ።*

ከቁ.3-4 ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ምን ብሎ ነው የሚናገረው?

ይህ የጳውሎስ አገላለጽ፣ ለጢሞቴዎስ ምን የሚሰጠው ጥቅም አለ ብለህ ታስባለህ?

ይህስ የሁለቱ ግኑኝነት ለእኛ በአሁኑ ጊዜ የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?

2. በቁ.5 ስለጢሞቴዎስና ስለ ቤተሰቦቹ የተገለጸው ሃሳብ ምንድነው?

"ግብዝነት የሌለበት እምነት" ሲል ምንማለቱ ነው?

መልካም አስተዳደግ በሰው ሕይወት የሚያመጣው ለውጥ ምንድነው?

ይህስ እውነት በአሁኑ ጊዜ እንዴት በሕይወታች ሊተረጎም ይችላል?

3. በቁ.6 ላይ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚያሳሳበው ስለ ምንድነው?

ጳውሎስ የተጠቀመው ምሣሌ ምንድነው? (አገር ቤት ፍም በአመድ ይሸፈንና ያድራል)

ጳውሎስ ይህን ምሣሌ ለመጠቀም ለምን አስፈለገው?

ሰው እግዚአብሔርን እንዳያገለግል እሳቱን የሚያዳፍንበት አመድ ምን ምን ይመስልሃል?

4. በጢሞቴዎስ ስጦታ ላይ እሳቱን ያዳፈነው አመድስ ምን ይመስልሃል (ቁ.7)?

ሐዋርያው ፍርሃትን ምን ብሎ ነው የሚጠራው?

ፍርሃት እንዴት ነው መንፈስ የሚሆነው?

ከፍርሃት መንፈስ ነጻ እንድንሆን ከጌታ የተሰጠን ምንድነው?

5. ቁ.8 ላይ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚያስጠነቅቀው ስለምንድነው?

ጢሞቴዎስ በጳውሎስና በጌታ ሊያፍር ያስቻለው (የሚያስችለው) ምክንያት ምን ይመስልሃል?

እኛስ *"በጌታና በወንጌል"* የምናፍርበት ጊዜ ይኖር ይሆን? ካለስ ለምን ይመስልሃል?

6. ከቁ.8-11 ይልቁኑ ምን እንዲያድደርግ ነው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚመክረው?

7. በቁ.12 ጳውሎስ ይህ ሁሉ መከራ እየደረሰበት ሊጸና ያስቻለው ምክንያት ምንድነው?

ጳውሎስ በድፍረት እንዲህ ሊል ያስቻለውስ ምክንያትስ ምንድነው?

8. “እስር ቤት” (ሰውም በስጋ ባይታሰር) ሰው እንደልቡ በነጻነት እንዳይመላለስ የሚወስነው ነገር ሁሉ እስር ነው፣ ለምሣሌ፦ ጤና፣ ማጣት፣ መረሳት፣ ወዘተ...

ግን በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ምን እንድናደርግ ነው ጳውሎስ የሚያሳስበን?

9. ከቁ.13-14 ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ሁለት ምክር ምንድነው?

ለጢሞቴዎስ የእነዚህ ሁለት ሃሳቦች (ምክር) ጥቅሙ ምንድነው?

10. ከቁ.15-18 ጳውሎስ በችግሩ ወቅት ያገጠመው ምንድነው?

ጳውሎስ ስለ ሄኔሲፎሩ ቤተሰቦች የተናገረው ምንድነው?

ከእነዚህ ቤተሰቦች የሚያስደንቅህና ልትፈልገው የሚገባ ባህርይ ምንድነው?

11. እስቲ አንድ ሰው አስብ፣ በተለያየ መንገድ የተቸገረ (እስር ቤትም ባይገባ)

ለዚያ ሰው እንደ ሄኔሲፎሩ ቤተሰቦች እንዴት ልትሆን ትችላለህ?

12. ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ለጢሞቴዎስ ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት ምንድነው?

13. በአሁንስ ጊዜ ጳውሎስ ለእኛ የሚያስተላልፍልን መልዕክትስ ምን ይመስልሃል?

14. ጳውሎስን በዚህ ሁሉ መከራ የጸናው (12) በጌታ ታማኝነት ነው።

አንተስ በምታልፍበት መከራ ሁሉ እንደ ጳውሎስ በታማኝነት እየጸናህና፣ ለሌሎችንም እያጸናህ ነው?

## ***የምንጸልይበት አርእስት***

ስለ ክርስቶስ በሚደርስብህ መከራ ሁሉ እንዲያበረታህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ።

በሁኔታዎች ሁሉ በደስታና በታማኝነት ጌታን እንድታገለግለው ጸልይ።

በመከራ የሚያልፉትን ማጽናትና መደገፍ እንድትችል ጌታ እንዲረዳህ ጸልይ። አሜን!!!

## ጥናት ሁለት

### *“የክርስቶስ አገልጋይ ባህርይ”*

**የምንባብ ክፍል፡ 2ኛጢሞ.2፡1-13**

***መግቢያ፡*** *ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የተቀበለውን የወንጌል አደራ ለታመኑ ሰዎች አደራ መስጠት እንዳለበትና፣ መንፈሳዊ ሕይወቱንም በእንዴት አይነት አቅጣጫ ሊመራ እንደሚገባ የሰጠውን ምክር እንመለከታለን።*

***ዓላማው*** *የክርስቶስ አገልጋይ በፍጹም ታማኝነት ጌታውን እንዴት እንደሚያገለግልና በተጨማሪም እርሱን የሚተኩ ሌሎች ታማኝ አገልጋዮችን ማፍራት እንዳለበት ለመገንዘብ።*

1. በቁ.1 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በምን እንዲበረታ ነው የሚመክረው?

   ለምን “በስጦታ በርታ” “በእውቀት በርታ” “በሃይል በርታ” አላለውም?

2. በቁ.2 ጢሞቴዎስ አደራ የሚሰጠው ነገርና፣ አደራ የሚቀበሉት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?

   አገልግሎትን ለታመኑ አደራ የመስጠት ጥቅም ምንድነው?

   አንዳንድ ጊዜ ሰዎች አደራን ለሌሎች መስጠት የሚከብዳቸው ሰምን ይመስልሃል?

   አደራን ከሌሎች ለመቀበል ምን ዓይነት ዝግጅት ያስፈልግሃል?

3. ከቁ.3-7 ጳውሎስ የጠቀሳቸው *ሦስት* ምሣሌዎች ምንድን ናቸው?

4. ጢሞቴዎስ ምን አይነት <u>ወታደር</u> እንዲሆን ነው የተጠየቀው? “3”

   “በጎ ወታደር” ብሎ ሲል ምን ማለት ነው?

5. በውትድርና የሚያገለግል ምን ይጠበቅበታል? “4”

   ወታደር እራሱን በሌላ ነገር የሚያጠላልፈው እንዴት ነው?

   በአሁኑ ጊዜ እኛስ በምን መንገድ እራሳችንን ልናጠላልፍ እንችላለን?

6. ጢሞቴዎስ ምን አይነት ***<u>አሰፖርተኛ</u>*** እንዲሆን ነው የተጠየቀው? “5”

   የሩጫው የውድድር ሕግ ምን ይመስልሃል?

   በእሩጫችን ጊዜ የውድድሩን ሕግ ማወቅ የሚጠቅመን ለምንድን ነው?

7. ጢሞቴዎስ ምን አይነት ገበሬ እንዲሆን ነው የተጠየቀው? “6”

   መጸሐፍ ቅዱስ የክርስትናን ሕይወት ከገበሬ ጋር የሚያመሳስለው ለምንድነው?

በክርስትና ሕይወታችን እንደ ትጉህ ገበሬ እንሁን ስንል ምን ማለታችን ነው?

በመጸሐፍ ቅዱስ (ትጉህ ገበሬ) ምሣሌ የሚሆነን ሰው ማነው? እንዴት?

8. በቁ.7 ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ ምን ሊያስገንዘበው የፈለገ ይመስልሃል?

9. ከቁ.8-10 ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድነው?

ከቁ.3-4 ሃሳብ ጋር ያላቸው ግኑኝነትት ምን ይመስልሃል?

10. ከቁ.11-13 ጳውሎስ በእምነቱ እንዲጸና የረዱት ሃሳቦች ምንድናቸው?

ይህን እውነት ለጢሞቴዎስ ሊነግረው ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ምን ይመስልሃል?

ይህን እውነት ማወቃችን እኛስ ለሕይወታችን ምን ይጠቅመናል?

11. እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ ሌሎች አገልጋዮችን ማፍራት ይጠበቅበታል።

በአመራር ላይ ካለህ ሌሎች አገልጋዮችን እያፈራህ ነው? ካልሆነስ ለምን?

በአመራር ላይ ካልሆንክ፣ አደራን ተቀብለሃል? ካልተቀበልህስ ለምን? ልትቀበልስ ዝግጁ ነህ?

12. ከቁ.3-7 ጳውሎስ የጠቀሳቸው ሦስት ምሣሌዎችን ተመልክተናል።

የእነዚህ ሦስት ምሣሌዎች ባህርይ እንዲኖርህ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?

## ***<u>የምንጸልይበት አርእስት</u>***

እግዚአብሔር የወንጌል አደራን ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል እንድትችል እንጸልይ።

አለቃውን ለማስደሰት እንደሚፈልግ ወታደር

የውድድሩን ሥርዓት እንደሚከተል ሯጭ

ተግቶ እንደሚሰራ ገበሬ እንዲያደርገን። አሜን!!!

## ጥናት ሦስት

## *"ክርስቶስ የተቀበለው ሠራተኛ"*

### የምንባብ ክፍል፦ 2ኛ ጢሞ.2፥14-26

**መግቢያ፦** *ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ከማይረባና ከማይጠቅም ክርክር እንዲርቅና ጌታን ከሚፈልጉ ጋር በመሆን ጽድቅን እንዲከታተል የጻፈለትን መልዕክት እንመለከታለን።*

**ዓላማው፦** ***የክርስቶስ እውነተኛ ሠራተኛ የእርሱንና የሌሎችን ሕይወት ከክፉና ከማይጠቅም ክርክር እንዴትና ለምን መጠበቅ እንደሚገባው ለመገንዘብ***

1. ቁ.14 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚያስጠነቅቀው ስለ ምንድን ነው?

   "በቃል እንዳይጣሉ" (እንዳይነታረኩ) ሲል ምን ማለቱ ነው?

   መነታረክ ለምንድነው የማይጠቅመው?

   የዚህ አይነት መነታረክ አጋጥሞህ ያውቃል? ያየኸው ጉዳትስ ምንድነው?

2. ከቁ.15-16 ጢሞቴዎስ በምን እንዲተጋና ከምን እንዲርቅ ነው የተመከረው?

   የእነዚህ ሁለት ሃሳቦች በጢሞቴዎስ ሕይወት መፈጸም የሚያመጣው ለውጥ ምንድነው?

3. ከቁ.17-18 የተነሳው የክርክር ዓይነት ምን ነበር?

   ለዚህ አይነት ክርክር የጢሞቴዎስ ሃላፊነት ምን መሆን ነው የሚገባው? "15"

   አንተስ በአሁን ጊዜ ከእንደዚህ አይነት ክርክር መራቅ ያለብህ ለምንድነው? "16"

4. የቁ.19 ሃሳብ ከዚህ በላይ ከተመለከትነው ጋር እንዴት ይገናኛል?

5. ከቁ.20-21ን በመመልከት በአንድ ትልቅ ቤት የሚገኙ እቃዎች ምንድናቸው?

   እነዚህ እቃዎች የሚውሉት ለምን ለምን ተግባር ነው? "20"

   ጳውሎስ እነዚህን ምሣሌዎች የተጠቀመው ምንን ለመግለጽ ነው?

   በክፍሉ መሠረት የከበረ እቃ ሰው የሚሆነው ምን ሲያደርግ ነው? "19"

   (አዲሱን ትርጉም ይመልከቱ)

6. ከቁ.22-24 ጢሞቴዎስ የተሰጠው ማስጠንቀቂያና ምክር ምንድነው?

   "ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ሽሽ" ሲል በክፍሉ መሠረት ምንን ለማመልከት ነው? "23"

   ከዚህ ሽሽቶ (ከክርክርና ከጥል) ምንን እንዲያዘወትር ነው የተመከረው? "22"

   ጌታስ ከሰው የሚጠበቀው ባህርይ ምንድነው? "24"

7. በቁ.25-26 እና በቁ.17-18 ላሉት ሰዎች እንኳን ጢሞቴዎስ ገር መሆን ያለበት ምክንያት ለምንድነው?

8. በዚህ ጥናት መሠረት ሰውን የከበረ እቃ የሚያሰኘው ከምን ሲ.ርቅ ነው? “19”

9. እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ሁልጊዜ የሚጠብቀው ምንድነው? “24”

10. ምንም ያህል ሰዎች ቢስቱ ልንጠነቀቅ የሚገው ነገርስ ምንድነው? “25-26”

## *የምንጸልይበት አርእስት*

ከማይጠቅም ክርክር አንተንና ሌሎችን እግዚአብሔር እንዲጠብቃችሁ ጸልይ

ለሳቱ ሰዎች እንኳን ገር እንድትሆንና ወደ ቀናው መንገድ መመለስ እንዲችሉ ጸልይላቸው

የማያሳፍር ሠራተኛ ሆነህ(ሽ) ሁልጊዜ እራስህን (ሽን) ለማቅረብ እንድትችል(ዪ) ጸልይ(ዪ)

በንጹህ ልብ እግዚአብሔርን ከሚጠሩ ጋር አብሮ ለማገልገልና ለመዋል እንድትችል(ዪ)

ጸልይ(ዪ)። አሜን!!!

## ጥናት አራት

## *"እግዚአብሔርን እየመሰሉ መኖር"*

**የምንባብ ክፍል፦2ኛ ጢሞ. 3፡1-17**

**መግቢያ፦** *ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በዚህ መጨረሻው ዘመን ጊዜ የሠዎች ባህርያት ምን እንደሚመስልና፣ እርሱም በዚህ ዘመን ውስጥ ሲኖር ምን ማድረግ እንዳለበት የመከረውን እንመለከታለን።*

**ዓላማው፦** *ጳውሎስ የነበረበትን ዘመን መጨረሻ ብሎ ከጠራው እኛ አሁን የምንኖርበት ዘመን እንዴት የቀረበ እንደሆነ ተገንዝበን፣ እግዚአብሔርና እየፈራንና እየታዘዝን፣ እንዴት ለመኖር እንደምንችል ለመገንዘብ።*

የመጨረሻው ዘመን ሲባል ቶሎ ወደ ሃሳብህ (ሽ) የሚመጣው ነገር ምንድነው?

ከቁ. 2-5 በዚህ መጨረሻ ዘመን ያሉ ሰዎች የሚታይባቸው ባህርያት ምንድናቸው?

ወደ አስራ ዘጠኝ የሚሆኑ ባህርያት ተዘርዝረዋል። በዝርዝር ተነጋገሩበት ምን ማለት እንደሆኑ?

በአሁኑ ዘመን የትኛው ባህርይ ጎሎቶ ይታይ ይመስልሃል? ለምንስ ይመስልሃል?

በቁ.4 መጨረሻ ላይ በተጻፈው መሠረት፣ የእነዚህ ባህርያት መከሰት ሊያስከትል ያስቻለበት ዋና ምክንያት ምንድነው?

4. ቁ.5 "የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ይህስ በአሁን ጊዜ በእንዴት ዓይነት መልክ ሊገለጥ ይችላል? ምሣሌ ስጥ

5. ከቁ. 6-7 በተጻፈው መሠረት

በየቤቱ ሲገቡ የአገባባቸው ሁኔታ የተገለጸው እንዴት ነው? ይህ ስለ ሰዎቹ ምን ያሳይሃል?

ሾልከው ገብተው የሚማርኩት ማንን ነው?

እነዚህስ ሴቶች በቀላሉ የሚማረኩት ለምንድነው?

6. ከቁ. 7-9 ጳውሎስ እንደ ምሣሌነት የተጠቀመባቸው ሰዎች እነማን ናቸው?

የእነዚህ ሰዎች ዋነኛው ችግርና ፍጻሜያቸውስ ምንደነው?

ከእነዚህ ሰዎች ሕይወት ተምረን ልናስወግደው የሚገባን አንድ ነገር ምን ይመስላሃል (ሽ)?

7. ከቁ.10-11 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚያስታውሰው ስለ ምንድነው?

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ይህን ሊነግረው ያስፈለገው ምክንያት ለምን ይመስልሃል?

8. ቁ.12-13 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚመክረው ስለ ምንድነው?

ጢሞቴዎስ ይህን መረዳቱ ጥቅሙ ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

ጢሞቴዎስ ሊሰደድበት የሚችልበት አንደኛው ምክንያት እነማን ስለ አሉ ነው? (ቁ.8ን)

ተመልከት (ቺ)

በአሁኑስ ጊዜ እኛ በምን ዓይነት መንገድ ልንሰደድ እንችላለን?

9. ከቁ.14-17 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ይህን ክፉ ዘመን በድል ሊወጣበት የሚችልበትን መንገድ የመከረው እንዴት ብሎ ነው?

10. ቁ.16-17 መሠረት የእግዚአብሔርን ቃል መማርና ማወቃችን የሚጠቅመን ለምንድነው?

11. በዚህ ባለንበት ክፉ ዘመን እግዚአብሔርን በመፍራትና በመታዘዝ እንድንኖር የሚረዳን በክፍሉ መሠረት ምንድነው?

12. እግዚአብሔርን መምሰል “ዋጋ ያስከፍላል” አንተ ወይስ አንቺ ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅታችኋል?

# ጥናት አምስት

## *“አደራን በታማኝነት ስለ መፈጸም”*

**የምንባብ ክፍል፦2ኛ ጢሞ. 4፡1-22**

**መግቢያ፦** *ሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወቱ ፍጻሜ በተቃረበ ጊዜ ለጢሞቴዎስ የወንጌል ሰባኪነትን ስራን አገልግሎት በታማኝት እንዲፈጽም የጻፈለትን መልዕክት እንመለከታለን።*

**ዓላማው፦** *ከጌታ የተቀበልነውን የሕይወትና የአገልግሎት አደራ በፍጹም ታማኝነት እስከመጨረሻው ድረስ እንዴት መፈጸምና ማጠናቀቅ እንደምንችል ለመገንዘብ።*

ሰዎች ጥብቅ አደራ ወይም ብርቱ ኃላፊነት ጥለውብህ ያውቃሉ? እንዴት ተወጣኸው (ሽው) ?

በቁ.1 መሠረት ጢሞቴዎስ እየተቀበለ ያለው አደራ የጠበቀና ብርቱ መሆኑን የምንገነዘበው እንዴት ነው?

ከጌታ የተቀበልከውን አደራ በዚህ መልኩ አይተኸው (ሽው) ታውቃለህ?

አዎን ከሆነ እንዴት አየኸው? አላየሁትም ከሆነ፣ ለምን አላየኸውም (ሽውም)?

በቁ.2 ላይ ጢሞቴዎስ እንዲፈጽመው የተሰጡት አደራዎች ምንድናቸው?

አስፈላጊነታቸውንና ትርጉማቸውን በዝርዝር ተወያዩበት

ከቁ.3-4 ድረስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚያስጠነቅቀው ስለምንድን ነው?

ሰዎቹ መስማት የሚፈልጉት ስለምንድነው?

የእግዚአብሔርን ቃል መስማት የማይፈልጉበትስ ምክንያት ለምንድነው?

ይህስ በአሁኑ ጊዜ በሕይወታችንና በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚታይ ይመስልሃል?

አዎን ከሆነ፣ በምን ዓይነት መልኩ የሚገለጥ (የሚታይ) ይመስልሃል? (ምሣሌዎችን ስጥ)

በቁ.5 መሠረት ጳውሎስ ጢሞቴዎስን አሁንም ደግሞ የሚያሳስበው ስለምንድነው?

እየደጋገመ የሚያሳስበው ለምን ይመስልሃል? ከዚህ እውነትስ እኛ ምን እንማራለን?

ከቁ.3-4 ድረስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሚነግረው ስለምንድነው?

ምን ማለት እንደሆነ እያንዳንዱን በዝርዝር ተወያዩበት፣

ጌታን ፊት ለፊት ለማየት ድፍረት የነበረው ለምን ይመስልሃል?

አንተስ አሁን ወደ ጌታ ብትጠራ እንደ ጳውሎስ በድፍረት ለማለት ትችላለህ?

ካልሆነስ፣ ይህ የጳውሎስ ሕይወት ምን እንድታደርግ ያስገነዝበሃል?

8. ቁ.13 ወደ ሕይወቱ ማብቂያ ላይ የደረሰ ቢሆንም ብራናውን እንዲመጣለት መፈልጉ ምን ስለ ጳውሎስ ያመለክተናል?

ቁ.11 "ማርቆስንም ይዘኸው ና ይጠቅመኛል" ማለቱስ? (ሐዋ.15፡37-40)

ቁ.13 "በርኖሱንስ" አምጣልኝ ሲል በምን ዓይነት ሁኔታ መኖሩን ያስገነዝበናል?

9. በዚህ ክፍል ጳውሎስና የተውትና የከፉበት ሰዎች እነማን ናቸው? ቁ.14-17፣ ቁ.9

ቁ.17 እንደዚህ እንኳን ቢያደርጉትም ጳውሎስ ስለ እነርሱ ያለው አመለካከት እንዴት ነው?

በዚህ ብቸኝነት ውስጥ ጳውሎስ ሊቆም የቻለው እንዴት ነው? ቁ.17-18 ተመልከት

እኛ በጳውሎስ ቦታ ብንሆን ምን የምናደርግ ይመስላችኋል?

10. ከቁ. 19-22 ባለው የመሰናበቻ ክፍል የተጠቀሱትን ሰዎች በተመለከተ ሐዋ. 18፡ 2-4 እና ሮሜ 16፡3-5 ተመልክታችሁ ተነጋገሩበት?

11. ይህ ክፍል ከጌታ የተቀበልነው አደራ እስከ ምን ድረስ ልንፈጽም እንደሚገባን ያስተምረናል?

12. ይህንንም ታላቅ አደራ ለመወጣት ልናደርገው የሚገባን ተቀዳሚው ተግባር ምንድነው?